መልእክት አምስት

## እግዚአብሔር በኢዮብ ዘንድ የነበረው ውጥን—መልካም ሰው አምላክ-ሰው እንዲሆን

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፡- ኢዮብ 1፥1፣ 8፤ 2፥3፣ 9፤ 27፥5፤ 31፥6፤ 42፥5-6

**I. ስልሳ ስድስት መጻሕፍት የያዘው መጽሐፍ ቅዱስ ለአንድ ነገር ብቻ ነው—ክርስቶስን እንኖረው እና ክርስቶስን እንገልጠው ዘንድ እግዚአብሔር ሕይወታችን፣ ባሕርያችን እና ሁሉ ነገራችን ለመሆን በክርስቶስ እንደ መንፈስ ራሱን ወደ እኛ ውስጥ ለማደሉ ነው—ኤፌ. 3፥16-17፤ ፊልጵ. 1፡21፡-**

ሀ. ይህ ሕይወታችንን የሚገዛ መርህ ሊሆን ይገባል—ዮሐ. 6፥57።

ለ. በተግባራዊ መንገድ፣ ይህ ለድስታችን የዛሬው የሕይወት ዛፍ ሊሆን ይገባል—ራእ. 22፥14።

**II. ኢዮብ በፍጹምነቱ፣ በቅንነቱ እና በሐቀኝነቱ ራሱን የሚገልጥ መልካም ሰው ነበር—ኢዮብ 27፥5፤ 31፥6፤ 32፥1፡-**

ሀ. ፍጹም መሆን ከውስጡ ሰው ጋር የተገናኘ ነው፣ ቅን መሆን ከውጪው ሰው ጋር የተገናኘ ነው—1፥1።

ለ. ኢዮብ ሐቀኝነት ያለው ሰው ነበር፤ ሐቀኝነት ፍጹም እና ቅን የመሆን ጥቅል ድምር ነው—2፥3፣ 9፤ 27፥5፤ 31፥6፡-

1. ከኢዮብ አንጻር፣ ሐቀኝነት እርሱ የሆነው ነገር ጥቅል መገለጥ ነው።
2. በጠባይ፣ ኢዮብ ፍጹም እና ቅን ነበር፣ በስነምግባሩ፣ ከፍተኛ ደረጃ ያለው ሐቅ ነበረው።

ሐ. ኢዮብ በአዎንታዊ መልኩ እግዚአብሔርን ፈራ፥ በአሉታዊ መልኩ ከክፋት ራቀ—1፥1፡-

1. እግዚአብሔር ሰውን የፈጠረው እንዲፈራው እና ምንም ስህተት እንዳይፈጽም ብቻ አልነበረም፤ ይልቁንም፣ ሰው እግዚአብሔርን ይገልጥ ዘንድ እግዚአብሔር ሰውን በመልኩ እንደምሳሌው ፈጠረው—ዘፍ. 1፥26።
2. እግዚአብሔርን መግለጥ እግዚአብሔርን ከመፍራትና ከክፋት ከመራቅ ይበልጥ ከፍ ያለ ነው።
3. ኢዮብ በፍጹምነቱ፣ በቅንነቱ እና በሐቀኝነቱ የደረሰበት ነገር ሙሉ በሙሉ ከንቱ ነበር፤ ያ የእግዚአብሔርን ዓላማ አልፈጸመም፣ የእግዚአብሔር መሻትንም አላረካም፣ ከዚህም የተነሣ ለኢዮብ በፍቅር ግድ ተሰኝቶ ነበር—ኢዮ. 1፥6-8፤ 2፥1-3።

መ. ኢዮብ የሚያስፈልገው ነገር እንደነበር የሚያውቀው እግዚአብሔር ብቻ ነበር—በውስጡ እግዚአብሔር አልነበረውም፤ ስለዚህ፣ እግዚአብሔር ለዓላማው መፈጸም ይገልጠው ዘንድ ኢዮብ እርሱን እንዲያገኝ ፈለገ—42፥5-6።

**III. የእግዚአብሔር ውጥን ኢዮብ እግዚአብሔርን በባሕርያቱ የሚገልጠው አምላክ-ሰው እንዲሆን ነበር—22፥24-25፤ 38፥1-3፡-**

ሀ. ኢዮብ በፍጹምነቱ፥ በጽድቁ እና በሐቀኝነቱ ከደረሰባቸው ነገሮች ምትክ እግዚአብሔርን ያገኝ ዘንድ እግዚአብሔር ኢዮብን ወደ ሌላ ክልል፣ ወደ እግዚአብሔር ክልል አስገባው—42፥5-6።

ለ. እግዚአብሔር በኢዮብ ዘንድ የነበረው ውጥን እርሱን መጨረስ፣ በፍጹምነትና በቅንነት በከፍተኛው የስነምግባር ደረጃ የደረሰባቸውን ነገሮች፣ ስኬቶቹን መግፈፍ ነበር—31፥6።

ሐ. የእግዚአብሔር ውጥን በእግዚአብሔር ተፈጥሮ እና ባሕርያት የታደሰ ኢዮብን ይገነባ ዘንድ ፍጹሙን እና ቅኑን ተፈጥሮአዊ ኢዮብ ማፈራረስ ነበር—1፥6-8፤ 2፥3-6።

መ. የእግዚአብሔር ውጥን ኢዮብን በክርስቶስ ለእግዚአብሔር መገለጥ የእግዚአብሔር ሙላት ይሆን ዘንድ የእግዚአብሔር አካል መልበስ በሆነው በክርስቶስ የተሞላ የእግዚአብሔር ሰው ማድረግ ነበር—1 ጢሞ. 6፥11፤ 2 ጢሞ. 3፥17።

ሠ. የእግዚአብሔር ኢዮብን መግፈፍና መጨረስ የተከናወኑት፣ ኢዮብን በእግዚአብሔር በራሱ መልሶ ለመገንባት መሠረት እና መንገድ ይኖረው ዘንድ እርሱን ለማፈራረስ ነበር፤ ይህም ኢዮብ እግዚአብሔርን ለመግለጥ የእግዚአብሔር ሰው፣ በተመሳሳኪነቱ ሳይሆን በሕይወቱና በባሕርይው ከእግዚአብሔር ጋር አንድ ዓይነት ይሆን ዘንድ ነው—ኤፌ. 3፥16-21።

**IV. በክርስቶስ እግዚአብሔር ወደ ሰው ውስጥ ተቀናብሯል፣ ሰው ወደ እግዚአብሔር ውስጥ ተቀናብሯል፣ እግዚአብሔር እና ሰውም አምላክ-ሰው ተብሎ የሚጠራው አንድ አካል ለመሆን በአንድ ላይ ተዋሕደዋል—ማቴ. 1፥21፣ 23፤ ሉቃ. 1፥35፤ ቲቶ 2፥13፤ 1 ጢሞ. 2፥5፦**

ሀ. ብዙ አምላክ-ሰዎች፣ የእግዚአብሔር ብዙ ልጆች የክርስቶስ፣ የመጀመሪያው አምላክ-ሰው መጨመር፣ ርቢ፣ ብዜትና መቀጠል ናቸው—ዮሐ. 12፥24፤ ዕብ. 2፥10፤ ሮሜ 8፥29።

ለ. አምላክ-ሰው የእግዚአብሔርን ሕይወትና ባሕርይ የሚካፈል፣ ከዚህም የተነሣ በሕይወቱና በባሕርይው ከእግዚአብሔር ጋር አንድ የሚሆን፣ በዚህም እግዚአብሔርን የሚገልጥ ነው—ዮሐ. 3፥15፤ 2 ጴጥ. 1፥4፤ 1 ቆሮ. 6፥17።

ሐ. አምላክ-ሰው የእግዚአብሔርን ሕይወትና ባሕርይ የያዘ የእግዚአብሔር ልጅ ለመሆን ከእግዚአብሔር ተወልዷል—ዮሐ. 1፥12-13፤ 3፥6፦

1. አምላክ-ሰው ሁለት ሕይወቶች፣ የሰብዕና እና መለኮታዊው ሕይወት፣ ሁለት ባሕርያት፣ ሰብዕና እና መለኮት አሉት።
2. አምላክ-ሰው የሕይወት-ሰው ነው—1 ዮሐ. 5፥11-13፤ ሮሜ 8፥2፣ 6፣ 10-11።
3. አምላክ ሰው የወርቅ-ሰው ነው—ዘጸ. 25፥11፤ 1 ጴጥ. 1፥7፤ ራእ. 3፥18፤ 21፥18።

መ. አምላክ-ሰው በእግዚአብሔር የተቀናበረ፣ እግዚአብሔር እንደ ሕይወቱ፣ የሕይወት አቅርቦቱ እና ሁሉ ነገሩ ያለው ነው፤ ስለዚህ፣ አምላክ-ሰው ሰው፣ ሆኖም አምላክ፣ አምላክ፣ ሆኖም ሰው ነው—ኤፌ. 3፥16-17።

ሠ. አምላክ-ሰው አዲስ ፍጥረት እና በክርስቶስ የእግዚአብሔር ጽድቅ ነው—2 ቆሮ. 5፥17፣ 21።

ረ. አምላክ-ሰው በማንነቱ ሁሉ፣ ከልቡ፣ ከነፍሱ፣ ከአእምሮው እና ከኃይሉ ጌታን ይወዳል—ማር. 12፥30።

ሰ. አምላክ-ሰው በሥጋ አይታመንም፣ ራሱን ይክዳል፣ ክርስቶስን ለመኖርም መንፈሱን ያንቀሳቅሳል—ፊልጵ. 3፥3፤ ማቴ. 16፥24፤ 1 ጢሞ. 4፥7፤ ፊልጵ. 1፥21።

ሸ. አምላክ-ሰው የእግዚአብሔር ቃል ያለው፣ የእግዚአብሔርን እስትንፋስ ወደ ውስጡ የሚተነፍስ የእግዚአብሔር ሰው ነው—1 ጢሞ. 6፥11፤ 2 ጢሞ. 3፥16-17።

ቀ. አምላክ-ሰው ኢ-ጥገኛ ግለሰብ እንዳልሆነ፣ ነገር ግን ከብዙዎች የሆነው አምላክ-ሰው—የክርስቶስ አካል፥ የአንዱ አዲሱ ሰው— ክፍል እንደሆነ ይገነዘባል—1 ቆሮ. 12፥12-13፤ ኤፌ. 4፥16፤ ቆላ. 3፥10-11።

*© 2026 Living Stream Ministry*